# የ2002 ዓ.ም አገራዊ ምርጫ ሂደትና ውጤትን አስመልክቶ ከኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) የተሰጠ መግለጫ

ኢዴፓ ምርጫ 97ን ተከትሎ በአገራችን በተከሰተው የፖለቲካ ቀውስ ምክንያት ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአገራችን ለመንግሥት ሥልጣን የሚበቁበት ዕድል ለብዙ ዓመታት ወደኋላ መመለሱን በተደጋጋሚ ሲገልጽ ቆይቷል። ገዢው ፓርቲም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በያዝነው የጥንፈኝነት ፖለቲካ ወደፊት የምንገፋበት ከሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሌሎች አሥርት አመታት በአንድ ብቸኛ ፓርቲ ፍጹማዊ የበላይነት እየተገዛ ሊቀጥል እንደሚችል ስጋታችንን በተደጋጋሚ ስንገልጽ መቆየታችንም ይታወሳል። ይህ የኢዴፓ ቅድመ ግምገማ ምን ያህል ትክክለኛ እንደነበር በዘንድሮ የምርጫ ውጤት ተረጋግጧል።

በዘንድሮ የምርጫ ውጤት የታየውን አሳዛኝና አስደንጋጭ ክስተት ምርጫ 97ን ተከትሎ ከተሰሩት ስህተቶች ነጥሎ ማየት አይቻልም። በአንድ በኩል ገዢው ፓርቲ ምርጫ 97ን ተከትሎ የተቀሰቀሰውን የሕዝብ ቅሬታ ከመጠን ባለፈ የኃይል እርምጃ በማፈኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በወቅቱ ከፍተኛ የሕዝብ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረው ቅንጅት የተሳሳተ የፖለቲካ ስልት በማራመዱ ምክንያት የአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት ወደፊት ከመራመድ ይልቅ ወደ ኋላ ሊቀለበስ ችሏል። ቅንጅት በወቅቱ የተፈጠረውን የሕዝብ የትግል ተነሳሽነት በአግባቡ ጠብቆ በመያዝ፣ በሙሉ ኃይሉ ፓርላማ ገብቶና አዲስ አበባ መስተዳድርን ተረክቦ ሰላማዊ ትግሉን አጠናክሮ ቀጥሎበት ቢሆን ኖሮ በዘንድሮው ምርጫ የታየው ውጤት በይዘትም ሆነ በቅርጽ እጅግ ከአሁኑ የተለየ በሆነ ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ካለፉት ስህተቶቻችንና ድክመቶቻችን በቀላሉ መማር ባለመቻላችን የዘንድሮው የምርጫ ውጤት የሰላማዊና የምክንያታዊ የፖለቲካ ኃይሎችን ጤናማ አቋም ሳይሆን "ኢትዮጵያ ውስጥ ሠላማዊ ትግልና የምርጫ ፖለቲካ አይሰራም" የሚል ጽንፈኛ አቋም የሚያራምዱ የፖለቲካ ኃይሎችን አመለካከት ለጊዜውም ቢሆን የሚያጠናክር ሆኖ አልፏል።

ኢዴፓ ከምርጫው ቀደም ብሎ ባደረገው ግምገማ በዘንድሮው ምርጫ መንግሥታዊ ለውጥ እንደማይመጣ ወደ እርግጠኛነት የተጠጋ ግምት የነበረው ቢሆንም አሁን በታየው መጠን ገዥው ፓርቲ ምርጫውን ሙሉ በሙሉ ያሸንፋል የሚል ግምት ግን ፈጽሞ አልነበረውም። ኢዴፓ በዘንድሮው ምርጫ አጠቃላይ ሂደት ላይ ባደረገው ግምገማ ሕዝቡና ተቃዋሚዎች ብቻ ሳንሆን እራሱ ገዥው ፓርቲም ከሚጠብቀው በላይ የአንድን ፓርቲ ፍፁማዊ የበላይነት የሚያረጋግጥ የምርጫ ውጤት ሊመጣ የቻለው በሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው ብሎ ያምናል።

1ኛ. ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ የመወዳደሪያ ሜዳውን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች የጠበበ እንዲሆን በማድረጉና በየወረዳውና በየቀበሌው ባሰማራቸው ካድሬዎቹ አማካኝነት በሕዝቡ ውስጥ ከፓርቲዎች የሥነ-ምግባር ደንብ የሚጻረርና ከመጠን ያለፈ የማዋከብ፣ የማስፈራራት፣ የሐሰት ቅስቀሳ የማካሄድና የተዛባ መረጃ የመስጠት ድርጊት በመፈፀሙ፣

2ኛ. ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተከፋፍለን ለምርጫ በመቅረባችንና የገዥውን ፓርቲ ሁለንተናዊ ተጽዕኖ ለመቋቋም የሚያስችል የስልት፣ የመረጃ ፍሰት፣ የሰው ኃይል፣ የድርጅታዊ መዋቅር፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ከፍተኛ ድክመት ያለብን በመሆኑ፤

3ኛ የተቃዋሚውን ጐራ የሚደግፈው አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል ፓርቲዎችን የሚደግፍበት መመዘኛ የተዛባ በመሆኑና ሰላማዊ ትግሉን በሙሉ ልብ ገና ያልያዘው በመሆኑ፣ ከዚህ በተጨማሪም ሕዝቡ ከሃሣብ ድጋፍ አልፎ በጉልበት፣ በጊዜ፣ በእውቀት፣ በገንዘብና በቁሳቁስ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በተግባር በማገዝ ረገድ ከፍተኛ ድክመት ያለበት በመሆኑ ነው፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት በተቃዋሚ ፓርቲዎችና ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በሚደግፈው ሕዝብ ዙሪያ የሚታዩ ድክመቶች ለምርጫው ውጤት የተዛባ መሆን የራሳቸው ድርሻና አስተዋጽኦ ያላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የዘንድሮው ምርጫ በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን ሰፊ የፖለቲካ የአስተሳሰብ ልዩነቶች በትክክል በማያንጸባርቅና ነጻና ፍትሃዊ ሊባል በማይችል ሁኔታ ሊጠናቀቅ የቻለው በዋናነት ገዥው ፓርቲ በፈጸማቸው ስህተቶችና ድክመቶች ነው ብሎ ኢዴፓ ያምናል፡፡

ኢዴፓ በምርጫው አጠቃላይ ሂደት የታዘባቸው ዋና ዋና ግድፈቶች በጥቅል የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ፓርቲዎች ከመንግሥት ያገኙት የገንዘብ ድጐማ ዘግይቶ የመጣና ፓርቲዎቹ ከሚያከናውኑት ተግባር በማይመጣጠን ሁኔታ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ፤
2. የመራጮች ምዝገባ የፓርቲዎች ክርክር ከመጀመሩ በፊት እንዲጠናቀቅ መደረጉ፤
3. በዕጩዎች ምዝገባ ወቅት ተቃዋሚዎች በቂ እጩዎች እንዳያቀርቡ የሚያደርጉ የማስፈራራት፣ በቤተሰብ በኩል ተጽእኖ የማሳደር፣ መደለያ የመስጠት፣ ተገቢ ያልሆኑ የምዝገባ መስፈርቶች የመጠየቅ ድርጊቶች መፈጸማቸው፤
4. የፓርቲዎች ክርክር ዘግይቶ የተጀመረ፣ ሁሉንም ርዕሰ ጉዳዮች በበቂ መጠን ያልዳሰሰ፣ ተቃዋሚዎች በቂ የሃሣብ ማቅረቢያ ጊዜ ያላገኙበት፣ ለአድማጮች በቀጥታ መተላለፍ ያልቻለ፣ ነጻ አወያዮች ያልመሩትና አድማጮች ፊት ለፊት ባልተገኙበት ሁኔታ የተካሄደ መሆኑ፤
5. በቴሌቪዥን ለሚሰራጭ የፓርቲዎች የምረጡኝ ዘመቻ የተመደበው ሰዓት አነስተኛ መሆኑ፤
6. በመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ለገዥው ፓርቲ የሚያደሉ የተለያዩ ፕሮግራሞች በምርጫው ወቅት ከመጠን በላይ እንዲሰራጩ መደረጋቸው፤
7. ተቃዋሚዎች በተለያዩ አካባቢዎች የሚያካሂዷቸው የምረጡኝ ዘመቻዎች ሚዛናዊና በቂ የዜና ሽፋን አለማግኘታቸው፤

8. ሕዝቡ ስለምርጫው በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው የሚያስችል የመራጮች ትምህርት በበቂ ሁኔታ አለመሰጠቱ፤

9. በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የሚገኙ የገዥው ፓርቲ አባላትና ካድሬዎች ለፓርቲዎች የሥነ-ምግባር ደንብ ተገዥ ባለመሆን በሕዝቡ ውስጥ አሰልቺ ውትወታ፣ ህገ-ወጥ ማስፈራራት መፈጸማቸውና ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በተመለከተ መሠረተ ቢስ ቅስቀሳ በሰፊው ማካሄዳቸው፤

10. የገዥው ፓርቲ አባላት ምርጫው ሚስጥራዊ እንዳልሆነና መራጮች ማንን እንደመረጡ በቀላሉ እንደሚታወቅ አድርገው በአርሶ አደሩ ሕዝብ ውስጥ በሰፊው መቀስቀሳቸው፤

11. የገዥው ፓርቲ አባላት ተቃዋሚዎች ቢመረጡ የአገሪቱ ሰላም እንደሚታወክ፣ የልማት ስራ እንደሚቋረጥ፣ እርዳታና ብድር ማግኘት እንደሚቀር፣ መሬት ከገበሬው ተነጥቆ ለከበርቴዎች እንደሚሰጥ አድርገው በሰፊው መቀስቀሳቸው፣

12. በአንዳንድ አካባቢዎች ህገ-ወጥ የሆነ ከዘረኝነትና ከኃይማኖት ጋራ የተያያዘ ቅስቀሳ መካሄዱ፤

13. ገዥው ፓርቲ አብዛኛዎቹን የአገሪቱን የመንግሥት ሠራተኞችና በመንግሥት በጀት የሚንቀሳቀሱ የልማትና የግንባታ ተቋማት ሠራተኞችን ከሥራ ዋስትናቸው ጋር በተያያዘ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሆኑ የሚያስገድድ ጫና መፍጠሩ፤

14. በገጠር አካባቢዎች የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች በኅብረተሰቡ ዘንድ እንደ ወንጀለኛ እንዲታዩና ማኅበራዊ መገለል ጭምር እንዲደርስባቸው የሚያደርግ ቅስቀሳ መካሄዱ፤

15. የመንግሥትና የፓርቲ ሥራን መለየት በማይቻልበት ሁኔታ የመንግሥት ገንዘብ፣ የመንግሥት የሥራ ሰዓት፣ የመንግሥት ተሽከርካሪዎችና የተለያዩ ቁሳቁሶች ለምርጫ ቅስቀሳ ጥቅም ላይ መዋላቸው፣ በአንጻሩ የተቃዋሚ ፓርቲ እጩዎችና አባላት የሆኑ የመንግሥት ሠራተኞች በምርጫው ወቅት የዓመት እረፍታቸውን እንኳ እንዳይጠቀሙ በብዙ አካባቢዎች መከልከላቸው፤

16. የሴፍቲኔት ፕሮግራም የአርሶ አደሩን ሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት በሚያስችል ሁኔታ በሰፊው የፖለቲካ መጠቀሚያ መደረጉ፤

17. በሕዝብ ታዛቢነትና በሲቪክ ማህበራት ስም በምርጫ ታዛቢነት የተሰማሩ በርካታ ሰዎች ከገዥው ፓርቲ ጋር ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ትስስር ያላቸው መሆኑ፤

18. በአገሪቱ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ምርጫውን ለማስፈጸም የተሰማሩ አብዛኛዎቹ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት ከገዥው ፓርቲ ጋር ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ትስስር ያላቸው መሆኑ፤

19. እድሮችን የመሳሰሉ የተለያዩ የሕዝብ ማህበራዊ ተቋሟት የፖለቲካ ድጋፍ ማሰባሰቢያ እንዲሆን መደረጋቸው፤

20. የምርጫ ቅስቀሳ መጠናቀቁ ከታወጀበት ቀንና ሰዓት በኂላ እስከ መጨረሻው የድምጽ መስጠት ሂደት ድረስ የገዥው ፓርቲ አባላት በየሰፈሩና በየምርጫ ጣቢያዎቹ ዙሪያ የምርጫ ቅስቀሳ ማድረጋቸው፤

21. በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍል የሕዝቡን በነጻነት የመምረጥ መብት በሚጋፋ ሁኔታ መራጮች አስቀድሞ በተወሰነላቸው ሰዓት በአምስት ሰው ተቧድነውና ማንን መምረጥ እንዳለባቸው የሚወስንላቸው አለቃ ተመድቦላቸው በጫና እንዲመርጡ መደረጋቸው፤

22. በአንዳንድ አካባቢዎች ከሕግ ውጭ ከአንድ በላይ የኢህአዴግ ወኪል ታዛቢዎች በየምርጫ ጣቢያው እንዲመደቡ መደረጉና በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች የተቃዋሚ ፓርቲዎች ወኪል ታዛቢዎች ያለአግባብ እንዲባረሩ መደረጉ፤

23. የድምጽ መስጫው ወረቀት የምልክት አቀማመጥ ገዥውን ፓርቲ በሚጠቅም አኳኋን አስቀድሞ መዘጋጀቱ፣

24. በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች ቀድሞ ከተመዘገበው መራጭ ሕዝብ ቁጥር በላይ ድምጽ የተሰጠበት ሁኔታ መከሰቱ፤

25. አንዳንድ የምርጫ አስፈጻሚዎች በምርጫው እለት ስለድምጽ አሰጣጡ ሥርዓት ሆን ብለው የተዛባ መረጃ ለሕዝብ መስጠታቸው፣

26. በገጠር አካባቢዎች ያለአግባብና ለገዥው ፓርቲ በሚጠቅም መንገድ የድምጽ መስጫ ወረቀቱ እየታጠፈ ለመራጮች እንዲታደል መደረጉ፣

27. በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች ቃለ-ጉባዔ ሳይያዝና በድምጽ መስጫ ወረቀቶች ላይ ፊርማና ማህተም አስቀድሞ ባልተቀመጠበት ሁኔታ ድምጽ እንዲሰጥ መደረጉ፤

28. በገጠር አካባቢዎች ድምጽ ለመስጠት የሌላ ሰው እርዳታ የማያስፈልጋቸው ሰዎች አስቀድሞ በተመደበ ሰው እርዳታ ሰጭነት ያለአግባብ ድምጽ እንዲሰጡ መደረጉ፤

29. በገጠር አካባቢዎች የድምጽ ቆጠራ ሲካሄድ ተገቢ ባልሆነ ሰበብ አስባብ ተቃዋሚዎችን የመረጡ ሰዎች ድምፅ ውድቅ እንዲሆን መደረጉ፤

30. የአንዳንድ ምርጫ ጣቢያዎች አዘገጃጀትና የምርጫ ቁሳቁሶች አጠቃቀም የምርጫውን ሚስጢራዊነት በአግባቡ የሚጠብቅ አለመሆኑ፣

31. የምርጫውን አጠቃላይ ውጤት ይቀይራሉ ተብሎ ባይገመትም በምርጫው እለት የተለያዩ የማጭበርበር ድርጊቶች በተለያዩ የምርጫ ጣቢያዎች መፈጸማቸው በምርጫው ሂደት የታዩ ዋና ዋና ጉድለቶችና ግድፈቶች ናቸው።

ከእነዚህ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ድርጊቶች በተጨማሪም በዚህ ዓይነቱ መድረክና መግለጫ ለሕዝብ ሊገለጹ አይገባም ብለን ያመንባቸው፣ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት

እያራመድነው የምንገኘውን የመቻቻልና የምክንያታዊነት መርህም ሆነ ሰላማዊ የትግል ስልታችንን የሚፈታተኑ የተለያዩ አጸያፊ ድርጊቶች መፈጸማቸውን አይተናል፡፡ በአጠቃላይ ኢህአዴግ በዘንድሮው ምርጫ መንግሥት የመሆን አብላጫ ድምጽ ከማግኘት አልፎ ከራሱም ግምት ውጭ ሁሉንም ተቃዋሚ ፓርቲዎች የፓርላማ መቀመጫ ለማሳጣትና በማንኛውም የዴሞክራሲ ሂደት ባልተለመደ ሁኔታ ከ99% በላይ የሆነ የፓርላማ መቀመጫ ለማሸነፍ የበቃበት ሚስጥር ሌላ ሳይሆን ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ድርጊቶች ምክንያት ኢህአዴግን በፈቃደኛነት ብቻ ሳይሆን በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ የመረጠ ቀላል የማይባል የኅብረተሰብ ክፍል ስለነበረ ጭምር ነው ብሎ ኢዴፓ ያምናል፡፡

በኢዴፓ እምነት ኢህአዴግ ምርጫውን በእርግጠኛነት ለማሸነፍ ከነበረው ከፍተኛ ጉጉትና ስጋት በመነጨ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ለሚገኙ አባላቱ "ኢህአዴግ መመረጥ አለበት" በሚል የሰጠው ግዳጅና ተልዕኮ ተገቢ ገደብ ያልተቀመጠለትና ጥንቃቄ የጐደለው ስለነበር የኢህአዴግ የበታች አባላት በበኩላቸው በመራጩ ሕዝብ ላይ የፈጠሩት ጫና ገደቡን አልፎ በምርጫው የአንድ ፓርቲን ፍጹማዊ የበላይነት ሊያስከትል የሚችል አስደንጋጭ ውጤት በአገሪቱ ሊከሰት ችሏል፡፡ ይህ ክስተት የአገሪቱ የፖለቲካ ምህዳር ከጊዜ ወደ ጊዜ የበለጠ እየሰፋ ሊሄድ ይችላል የሚል ጽኑ ተስፋ ለነበረን የፖለቲካ ኃይሎች ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ፋና ወጊ ለሆነውና በዚህም ድርጊቱ ሲመካ ለኖረው ለኢህአዴግም እጅግ ፈታኝ ክስተት ሆኗል፡፡ ኢህአዴግ ይህንን ክስተት እንደ ከፍተኛ የድል ውጤት እንጂ እንደ አደጋ ያላየው ቢሆንም ኢዴፓ ክስተቱን በሰላማዊ የፖለቲካ ኃይሎችና በአጠቃላይ በአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት ላይ የተጋረጠ ከፍተኛ አገራዊ አደጋ አድርጐ አይቶታል፡፡

ከ5 ዓመት በፊት የምርጫ 97ን ውጤት ተከትሎ በአገራችን በተፈጠረው የፖለትካ አጣብቂኝ ኢዴፓ በወቅቱ ተወዳጅነት የነበረውን ሳይሆን ትክክለኛ ነው ብሎ ያመነበትን አቅጣጫ በመከተል ለሰላማዊ ትግሉ መቀጠል ቀላል የማይባል ዋጋ ከፍሏል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመስመሩን ትክክለኛነትና የሃሣብ የበላይነቱን በሕዝቡ ዘንድ እያረጋገጠ የመጣው ኢዴፓ ዛሬም እንደገና በጽናትና በስክነት ሊያልፈው የሚገባ አዲስና ከባድ ፈተና ገጥሞታል፡፡ ኢዴፓ በዘንድሮው ምርጫ በተካሄዱ የምርጫ ክርክሮች የሃሣብ የበላይነት ያሳየ ፓርቲ ሆኖ እያለ በዚህ ምርጫ ምንም ዓይነት የምክር ቤት መቀመጫ ሳያገኝ መቅረቱ በአገራችን ዛሬም እንደትናንቱ ከምክንያታዊ የፖለቲካ አመለካከት ይልቅ የጽንፈኝነት የፖለቲካ አመለካከት የበለጠ ቦታ እያገኘ ሊመጣ እንደሚችል አዲስ ስጋት ፈጥሯል፡፡ የዘንድሮው ምርጫ ይዞት የመጣው ውጤት የተቃዋሚ ፓርቲዎችን መሸነፍ ብቻ ሳይሆን እራሱ የዴሞክራሲ ሂደቱ በአገራችን ተሸናፊ እየሆነ መምጣቱን የሚያሳይ በመሆኑ እንደ አንድ አገራዊ አደጋ ሊታይ የሚገባው ነው ብሎ ኢዴፓ ያምናል፡፡

ከዚህ አጠቃላይ ግንዛቤ በመነሳትም ኢዴፓ ከዚህ አገራዊ ችግር ለመውጣት ያስችሉናል ብሎ ያመነባቸውን የሚከተሉትን አቋሞች ለመውሰድ ተገዷል፡፡ እነዚህን አቋሞች ኢዴፓ ከሚያራምደው የምክንያታዊ ፖለቲካና በአጠቃላይም የ3ኛ አማራጭነት ሚና አንጻር ማጤንና መገንዘብ ተገቢ ይሆናል፡፡

1. በዘንድሮው ምርጫ ኢዴፓም ሆነ ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ ከሚጠብቀው በላይ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሙሉ በሙሉ የምርጫ መቀመጫ ያሳጣና አገሪቱ በአንድ ፓርቲ ብቸኛ የበላይነት ሥር እንድትወድቅ ያደረገ አስደንጋጭና አስገራሚ

የምርጫ ውጤት የመጣው በዋናነት በሌላ የተለየ ምክንያት ሳይሆን ከላይ በዝርዝር ባስቀመጥናቸው ጉድለቶችና ስህተቶች ምክንያት ነው። ገዥው ፓርቲ በዚህ ረገድ የሠራቸውን ስህተቶች በግልጽ አምኖ መቀበልና እንዲህ ዓይነቱ ስህተት ዳግም በአገራችን እንዳይደገም የሚያስችል ቁርጠኛ የእርምት እርምጃ መውሰድ ይገባዋል። ገዥው ፓርቲ በአስቸኳይ ከተቃዋሚዎች ጋር ለድርድር በመቀመጥም የአገሪቱን የምርጫ ሕግ፣ የአገሪቱን የዴሞክራሲ ተቋማት፣ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን አጠቃቀምንና የፓርቲዎች የገንዘብ ድጐማ አሠራርን በተመለከተ ተጨባጭ ለውጥ የሚያስከትል ስምምነት ላይ መድረስ ይጠበቅበታል። በዘንድሮው ምርጫ የታዩት ጉድለቶችና ድክመቶች በወሳኝ መልኩ መፍትሄ ካላገኙ በስተቀር ወደፊት በአገራችን ሊካሄዱ የሚችሉ ምርጫዎችም ነጻና ፍትሃዊ የመሆን እድላቸው አጠያያቂ ሆኖ መቀጠሉ አይቀርም።

2. ተቃዋሚ ፓርቲዎች በበኩላችን ከወቅቱ አስቸጋሪ ሁኔታ ለመውጣት የምናራምዳቸው አቋሞችና ስልቶች በአንድ በኩል የሰላማዊ ትግሉን ቀጣይነት ጥያቄ ውስጥ የማያስገቡና ሕዝቡን ተስፋ የማያሳጡ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከተፈጻሚነት የራቁ ሆነው የራሳችንን የትግል እንቅስቃሴ የበለጠ አጣብቂኝ ውስጥ የሚያስገባ ውጤት እንዳያስከትሉ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅብናል። ተቃዋሚዎች በዘንድሮው ምርጫ የገጠመን ከፍተኛ ሽንፈት ኢህአዴግ በፈጸማቸው ተገቢ ያልሆኑ ጫናዎች ብቻ ሳይሆን በራሳችንም ውስጥ ባሉ መሠረታዊ የአስተሳሰብና የድርጅታዊ ድክመቶች የመጡ መሆኑን ተገንዝበን እራሳችንን በድፍረት መገምገምና ድክመቶቻችንን አርመን ተጠናክረን የምንወጣበትን ስልትና አቅጣጫ መንደፍ ይኖርብናል። በተበታተነና እርስ በርስ በመናቆር እያካሄድነው ያለው ትግልም በሂደት የሕዝቡን ድጋፍ እያሳጣን መምጣቱን በመገንዘብም ተመሳሳይ የፖለቲካ ባህል፣ ርዕዮተ-ዓለምና አደረጃጀት ያለን ፓርቲዎች አብረን ለመሥራት የሚያስችለንን ጥረት ከወዲሁ መጀመር ይኖርብናል። ይህንን ማድረግ ከቻልን ትግላችን በአጭር ጊዜ እንደገና የዕድገት እመርታ የማያሳይበት ምክንያት አይኖርም። ይህንን ማድረግ ካልቻልን ደግሞ የምንመኘው ውጤትና ድል የበለጠ ከእኛ እየራቀ እንደሚሄድ አያጠራጥርም።

3. በዘንድሮው ምርጫ በአገራችን እየተካሄደ የሚገኘው የሰላማዊ ትግልና የምርጫ ፖለቲካ ከፍተኛ አደጋ ገጥሞታል ብሎ ኢዴፓ ያምናል። ነገር ግን የአንድ ሰላማዊ ፓርቲ ጥንካሬ የሚለካው በዚህ ዓይነቱ አስቸጋሪ ወቅት ትክክለኛ አቋም ወስዶ እንደገና ተጠናክሮ መውጣት በመቻሉ ነው ብሎ ያምናል። ስለሆነም ኢዴፓ በአሁኑ ወቅት የገጠመው ችግር ሰላማዊ ትግሉን የበለጠ በጽናት አጠናክሮ እንዲቀጥልበት እንጂ ከቶውንም ተስፋ እንዲቆርጥ ወይንም ሰላማዊ አቅጣጫውን እንዲለቅ የሚያስገድደው አይሆንም። ኢዴፓ ዛሬም በአገራችን መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚቻለው በአመጽና በጦርነት ሳይሆን በሰላማዊ ትግልና በምርጫ ፖለቲካ ብቻ ነው ብሎ ያምናል። ይህንን እምነቱንም የበለጠ አጠናክሮ ይቀጥልበታል። ከምርጫ 97 በኋላ የገጠመውን ፈተና ሁሉ በጽናት ተቋቁሞ አፈር ልሶ እንደገና መነሳቱን ያረጋገጠው ኢዴፓ ወደፊትም ይህንን የጽናት ልምዱን ተጠቅሞ ለከፍተኛ ውጤት እንደሚበቃ ቅንጣት ያህል አይጠራጠርም።

4. ተቃዋሚ ፓርቲዎች እየተጠናከርን ከመሄድ ይልቅ በሂደት እየተዳከምን እንድንመጣ ያደረገን አንዱ ተጨማሪ ምክንያት ደጋፊያችን ከሆነው የኅብረተሰብ ክፍል እያገኘነው ያለው ድጋፍ ከሃሣብ ድጋፍ አልፎ በበቂ መጠን በተግባራዊ ተሳትፎ የማይገለጽ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ደጋፊያችን የሆነው ኅብረተሰብ በአሁኑ ወቅት በደረሰብን አደጋ ሳይደናገጥና ተስፋ ሳይቆርጥ በተሻለ እልህና በአዲስ ተነሳሽነት አስፈላጊውን የተግባር ድጋፍና ተሳትፎ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የለውጥ ፍላጐት እንዲሁ በምኞት ብቻ እንደማይሳካ ደጋፊያችን የሆነው ሕዝብ የጠራ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል፡፡ የመራጭነት ካርድ እንኳ ሳያወጡ ዝንብሎ በተቃዋሚዎች ላይ ትችት መዘንዘር ከአንድ ለውጥን ከሚፈልግ ዜጋ የማይጠበቅ ተግባር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

5. ኢህአዴግ ምርጫውን ሙሉ በሙሉ በሚባል መጠን ያሸነፈ ቢሆንም በአገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከተቃዋሚዎች ጋር አብሮ የመሥራት ፍላጐት ያለው መሆኑን ሰሞኑን ይፋ አድርጓል፡፡ ይህ የኢህአዴግ " የአብረን እንሥራ" ጥሪ ከአሁን በፊት ይታይ እንደነበረው ለዲፕሎማሲና ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሳይሆን ለመስጠትና ለመቀበል መርህ ተገዢ የሆነ ልባዊ ጥያቄ ሆኖ ከተገኘ ኢዴፓ በጋራ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ምንጊዜም ከገዥው ፓርቲ ጋር ተባብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆኑን ዛሬም በድጋሜ ያረጋግጣል፡፡

6. በመጨረሻም ለአለፉት አምስት ዓመታት በኢዴፓ ላይ ሲካሄድ የነበረውን የአሉባልታ ዘመቻ ሰብራችሁ በመላው አገሪቱ ድምጻችሁን ለኢዴፓ ለሰጣችሁ ደጋፊዎቻችን በሙሉ ምስጋናችንን በዚህ አጋጣሚ እናቀርባለን፡፡ በዘንድሮው ምርጫ በከፍተኛ ተጽእኖና ጫና ኢህአዴግን ለመምረጥ የተገደዱ በርካታ ዜጐች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በቁጥር ቀላል የማይባል የአገራችን ሕዝብ በራሱ እምነትና ፍላጐት ኢህአዴግን የመረጠ መሆኑን ኢዴፓ በሚገባ ስለሚገነዘብ የዚህን ሕዝብ ድምጽ በሙሉ ልብ የምናከብር መሆኑን እየገለጽን በዚህ መንገድ ድምጽ አግኝታችሁ ለመመረጥ ለበቃችሁ አካላት መጭው አምስት ዓመት ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም የምትሠሩበት መልካም ጊዜ እንዲሆንላችሁ ኢዴፓ መልካም ምኞቱን በዚህ አጋጣሚ ይገልጻል፡፡ ኢዴፓ በምርጫው ሂደት ሞራልን የሚፈታተኑ በርካታ አሳዛኝ ድርጊቶችን የታዘበ ቢሆንም ስለሰላምና አገራዊ ጥቅም ሲባል ከጊዜያዊ ስሜታዊነት በመቆጠብ የሀገርንና የህዝብ ጥቅምን ማስቀደም ወቅቱ የሚጠይቀው እርምጃ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ ስለሆነም የፖለቲካ ፓርቲዎች አሸናፊነታችንንም ሆነ ተሸናፊነታችንን ከስሜታዊነት በፀዳ መንፈስ በአግባቡ እንድንይዘው በዚህ አጋጣሚ ኢዴፓ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**ግንቦት 23 ቀን 2002 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**
**የኢዴፓ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ**
**ኢዴፓ የወደፊቱ ፓርቲ!**